# የድጋፍ ምሽት በቶሮንቶ

የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ኢህአፓ የሰሜን አሜሪካ አህጉራዊ ኮሚቴ ድርጅቱ እያካሄደ ያለውን ፀረ ወያኔ ትግል ወደቀጣዩ ደረጃ ማሸጋገር ይረዳ ዘንድ ከፍተኛ የገንዘብ ማሰባሰብ ዘመቻ በማካሄድ ላይ መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ዕቅድ እውን ለማድረግ በተለያዩ ከተሞችና አካባቢዎች የሚገኙት የድርጅቱ አካላትና መዋቅሮች የተለያዩ የርዳታ ማሰባሰብ ፕሮግራሞች እያካሄዱ ይገኛሉ።
በዚሁም መሰረት በቶሮንቶና አካባቢው የሚገኘው የኢህአፓ ሀገር አድን ዘመቻ ኮሚቴ በ ኤፕሪል 14, 2013 በላሊበላ ሬስቶራንት ከምሽቱ 12 ሰአት (6፡00 ፒ ኤም) ጀምሮ የደጋፊዎች እርዳታ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አካሂዷል። በዚሁ እስከ እኩለ ሌሊት በዘለቀው ዝግጅት በከተማዋ የሚገኙ የፓርቲው ደጋፊዎችና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተገኙ ሲሆን በዝግጅቱ መግቢያ ላይ የኢህአፓ ሰሜን አሜሪካ ክፍል ይህንኑ ሀገር አድን ዘመቻ ለማካሄድ ያስተላለፈው መልእክት በንባብ ተሰምቷል። ከ እራት በኋላ በነበረው ጊዜ የዝግጅቱ ታዳሚዎች ትግሉን በተመለከተ የሀሳብ መለዋወጥ አካሂደዋል። በተጨማሪም በዝግጅቱ ላይ የተገኙት ወገኖች ወደፊትም ትግሉን ለመርዳት የሚቻላቸውን እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል። እንደሚታወቀው ሀገርን የማዳን ተልእኮን ያህል ከፍተኛ ግዳጅ ከግብ ለማድረስ ከፍ ያለ የገንዘብና ቁሳዊ ሀይል ይጠይቃል። የትግሉ ደረጃ ባደገ መጠንም ይኸው የገንዘብና ቁሳቁስ አስፈላጊነት ተመሳሳይ በሆነ መጠን ማደጉ የሚጠበቅ በመሆኑ ይህን አይነቱ ዝግጅት ወደፊትም በተጠናከረ መንገድ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህ አጋጣሚ በዝግጅታችን ላይ በመገኘት የተቻላቸውን ሁሉ ላደረጉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከፍተኛ ምስጋናችንን ስናቀርብ እንደወትሮው ሁሉ ወደፊትም ይኸው ወገናዊ ድጋፋቸው እንደማይለየን ተስፋችን ፅኑ ነው።

በሀገር አድን ዘመቻው በመሳተፍ ፀረ ወያኔውን ትግል እናግዝ
ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

በቶሮንቶ የኢህአፓ ሀገር አድን ዘመቻ ኮሚቴ